*“የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።”* 2ኛ ጢሞ 3፥16-17




ቦስተን የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የሥነ-ጽሑፍ አገልግሎት
በሁለት ወር አንድ ጊዜ እየተዘጋጀ የሚቀርብ መንፈሳዊ ጋዜጣ

# በውስጥ ገጾች

- ዕርሰ አንቀጽ፤
  - የዘመኑ ፍጻሜ እና የእግዚአብሔር ሃሳብ፤
- የሁለት ዓለም ሰዎች፤
  - ድንገት የታወረ አይናቸው ተገልጦ ያሉበትን ቢቃኙ ታዳኙ አዳኝ ሆኖ አገኙት፤አቤት የሁለት አለም ሰው ኑሮ ልዩ ነው፤ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።
- ጉዳዩ ከልብ ነው፤
  - እና እኛም በዚህ ዘመን ልናስተውለው የሚገባን ጌታ የልብ አምላክ
- ትዳር ምንድን ነው?
  - አንድ ጊዜ ለራሴ እንዲህ አልኩ እግዚአብሔር አዳምን ብቻውን ፈጥሮ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ያለው ተሳስቶ ነው እንዴ? ደግሞ ሔዋንን ከጎኑ በወሰደው አጥንት ሴት አድርጎ የሰራት ስህተቱን ለማስተካከል ነው እንዴ?
- የምለው አለኝ
  - ተማርኬአለሁ ገዝቶኛል ፍቅሩ
    ለየት ብሎብኝ ካየሁት ሁሉ፤
    ከዚህ የተነሣ ቃል ገብቼአለሁ
    ለሌላ ላልሆን እጅ አንስቼአለሁ፤
- ቃሌን አልዘነጋም፤
  - ባላየሽው ነገር ተስፋን እየሰነቅሽ ሳትጠቀሚበት በዚህ አፍላ እድሜሽ፤
  - ኢየሱስ ኢየሱስ እያልሽ ኋላ ቀረሽ በጣም አሳዘንሽኝ ስንቱ አመለጠሽ፤

በቦስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የምታምን የክርስቶስ ኢየሱስን የማዳን ወንጌል ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የምታሰራጭ ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህም ጋዜጣ ወንጌልን ከምታሰራጭባቸው መንገዶች አንዱ ሲሆን በቤተ ክርስቲያን የሥነ-ጽሁፍ አገልግሎት አባላት እየተዘጋጀ በየሁለት ወር አንድ ጊዜ ይቀርባል።

የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ
ፓስተር ምሕረቱ ሌጀቦ

**Email: Meheretu2614@yahoo.com**
**Telephone: 617-792-5764**

ዋና አዘጋጅ ..........ሄኖክ ተሾመ
ምክትል አዘጋጅ........ ሐብታሙ አስረስ
የውብዳር ፍሰሐ
ኮምፒዩተር ዝግጅት.... ትርሲት ጥላሁን
የፊት ገጽ ዲዛይነር...ዘነበ ምትኩ

ለቀጣዩ እትም ይረዳ ዘንድ የእናንተ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ስላለው በሚቀጥለው አድራሻ ያላችሁን አስተያየትና ጥያቄ ላኩልን።

አድራሻ:

Ethiopian Evangelical Church in Boston
88 Tremont Street
Boston, MA 02108
Tel. 617-816-8827
E-mail: Henokekka@yahoo.com

## <u>ርዕሰ አንቀጽ፤</u>

## <u>የዘመኑ ፍፃሜና የእግዚአብሔር ሐሳብ፤</u>

ዘመኑ እየተፈጸመ ስለመሆኑ እግዚአብሔር በቃሉና በመንፈሱ ከመቼውም ይልቅ በሚናገረው ትውልድ መካከል እንገኛለን። በዙሪያችን የምናያቸውም ሆኑ በዚህ ትውልድ መካከል እየሆነ ያለውና ሊሆን ወዳለው ነገር የሚሄድበት አቅጣጫ የሚሰጠን ምልክት ቢኖር ይኸንኑ ነው።

አዎን ለዘመኑ ምልክት ተሰጥቶታል፤ እንዲሁም ለእኛ ዘመኑን የምንመረምርበት፤ ከትውልድ ጥፋት የምናመልጥበት ቃል ተሰጥቶናል። ደቀመዛሙርት ጌታን "ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድን ነው?" (ማቴ 24፡3) ባሉት ጊዜ በምላሹ ከሰጣቸው ምልክት አንዱ "ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል" (ማቴ 24፡14) ያላቸውን በዘመናችን ከሚሆነው ጋር በማስተያየት ልናስበው ይገባል።

በዚህ የዘመን ፍፃሜ የእግዚአብሔር እቅድ ምን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ያለውን ሃሳብ ነው። ይኸን ሃሳቡን የሚፈጽመውም በልጁ በገዛው በራሱ ህዝብ ነው። ልብ ስንለው እግዚአብሔር ለዚህ ዓላማ ለራሱ ለይቶ የሚጠቀምበት ትውልድ አካል ነን። ከዚህ የሚበልጥ እድል ይኖር ይሆን?

ስለዚህ ይኸንን ታላቅ ኃላፊነት ለመወጣት ምን እንደሚጠበቅብን ቆም ብለን ልናስብ ይገባናል። ከሁሉ ይልቅ ፈጥነን ወደ ቃሉና ወደ መንፈሱ የምንመለስበት ጊዜ ቢኖር አሁን ነው። ጌታን ደስ የሚያሰኘውን በቃሉ እየመረመርን ልንመላለስ፤ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር ባለመተባበር ራሳችንን ልንጠብቅ ይገባናል። ይኸንን በእለት ኑሮአችን ስንገልጸውም ከላይ ለተጠቀሰው የእግዚአብሔር እቅድ ተካፋዮች ያደርገናል። ብንጨክን፤ ራሳችንንም ብንሰጠው፤ ለዚህ ዓላማ ከዚህ ክፉ ትውልድ መሃል የጠራን ጌታ በህይወታችን ሊሰራ የታመነ ነው !!

በወርቅነህ ተስፋዬ



# የቤተሰብ አምድ

## ትዳር ምንድን ነው?

ለመሆኑ ትዳር ማለት ምን ማለት ነው? ብዙ ሰዎችስ ትዳር ለምን ይመሰርታሉ? እግዚአብሔርስ ለምን ትዳር ይሰጠናል? በነዚህ ሃሳቦች ዙሪያ ብዙ እንደተጻፈ ብዙም እንደተባለ ብዙም ሊባል እንደሚችል አውቃለሁ። ነገር ግን ዛሬ ብእሬን እንድሰብቅ ያስገደደኝ ብዙ ሰዎች ጋብቻ ለመመስረት ሊወጥኑ መነሻ የሆነችው ሃሳብ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ትዳርን ከሰጠበት ዓላማ ጋር በእጅጉ የሚቃረን ሆኖ መገኘቱ ነው። ከዚህም የተነሳ ይህ ትውልድ ትዳር የተሳካለት ሲሆን አለማየታችን የተለመደ ነገር ሆኗል። ብዙ ወጣቶች ጋብቻ ለመመስረት ሲወጥኑ ዓላማቸውና ራዕያቸው እጅግ የተበላሸ በመሆኑ ትዳር በያዙ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለፍቺ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ ይታያሉ። በትውልዱ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ መርዙን እየረጨ ያለው በተጣጣመ መንገድ ትዳር የመያዝ አዝማሚያ ሥር ሳይሰድ መቀጨት ያለበት አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ይህንን ስል ግን ሁሉ ተሳስተዋል ማለቴ አይደለም።

እስኪ ለጽሑፌ መነሻ ይሆነኝ ዘንድ አንዳንድ ገጠመኞቼን ላውጋችሁ። ጊዜው ትንሽ ሰንበት ብሏል አንድ ሰው እንዲህ ሲል አጫወተኝ ብቸኝነቱ ባዶ ቤት ከፍቶ መግባቱ ሰልችቶኛል፤ ጌታ ቤቴን ከፍታ አልጋውን አነጣጥፋ ቡና አፍልታ ሞቅ ሞቅ አድርጋ የምትጠብቀኝ ሚስት በሰጠኝ አለኝ፤ በጥያቄው በጣም ነው የተገረምኩት እናም ወንድሜ ሠራተኛ ወይም ሚስት ምንድ ነው የምትፈልገው አልኩት ደግሞም አንድ እውነት ልንገርህ እግዚአብሔር በዚህ ግንዛቤ ውስጥ ሆነህ ሚስት አይሰጥህም ጥሩ ሠራተኛ ግን ሊሰጥህ ይችላል ብዬው ተለያየን። እንግዲህ ይህ ሰው ጋብቻ ለመያዝ የተነሳበትን አሳብ ልብ በሉ፣ ሚስት የሚሻው ሥራ ውሎ ሲመጣ ቤቱ ጭር ስለሚልበት ሞቅ ሞቅ አድርጋ እንድትጠብቀው ነው አይደንቅም ለዚህ ሰው ትዳር ከዚህ የዘለለ ዓላማ የለውም፣ እንግዲህ በዚህ መንፈስ የተመሰረተ ትዳር ምን ሊሆን እንደሚችል እናንተው ገምቱት።

አንዴ ደግሞ አንዱ ያለኝን ልንገራችሁ፣ ይህንን ሰው እንዲህ ስል ጠየኩት፤ ትዳር ለምን ትይዛለህ? የሰጠኝ መልስ በእጅጉ ነው ያስገረመኝ፤ የሚገርመው ትዳር ለመያዝ በተነሳበት አሳብ ላይ ትክክል ለመሆኑ አንዳች ጥርጥር የለውም፤ እንዲህ አለኝ "ጊዜው ክፉ ነው ኤድስም ብዙ ሕዝብ ጨርሷል፤ ከጊዜም ብዛት መውደቅ ሊመጣ ይችላል በጊዜ ሰብሰብ ማለት ነው" አለኝ፤ በጣው ነው የተደነኩት፤ በእርግጥ የነገረኝን ምክንያት ልቀበለው ብችልም እኳን ትዳር በዚህ መረዳትና በነዚህ ዓላማዎች ላይ ነው እንዴ መመስረት ያለበት? መነሻው ሃሳቡ ትክክል ነው? በፍጹም ስህተት ነው። ሌላ አንድ ገጠመኜን ልጨምርላችሁና ወደ ዋናው ሃሳቤ ልውሰዳችሁ፤ አንድ ወዳጄ ነው አንድ ቀን እንዲህ ሲል ጠየቀኝ አንተ ግን ለምን አታገባም? አገባለሁ ጌታ ከእሱ የሆነች እህት እስኪሰጠኝ ጊዜ ወስጄ እየጸለይኩበት ነው አልኩት፤ አፍታም አልሰጠኝ ከአፌ ነጠቅ አድርጎ ምን ነካህ ይሄ አሁን ምን ጊዜ መውሰድ ያስፈልገዋል በዙሪያህ ካሉ ሴቶች መረጥ መረጥ አድርገህ እንደኔ ላፍ ነው እንጂ! አለኝ ባራድኛ ፤ ወንድሜ ይሄ እኮ የእድሜ ልክ ጉዳይ ነው ግሮሰሪ ገብተህ ከመደርደሪያ ላይ መርጠህ የምትገዛው ሸቀጥ አይደለም ብለው አንተ ደግሞ በጣም ታከራለህ ይልቅ አየት አየት አድርገህ የቆጠረችውን (ገንዘብ መሆኑ ነው) ለቀም ማድረግ ነው እንጂ እከሌን እከሌን አታይም ይለኝ ጀመር በጊዜያዊ ጥቅም ተስበው ሚስት ሳይሆን መኪና፤ ቤት፤ ሱቅ ያገቡ ሰዎች እየቆጠረልኝ፤ በል ይበቃሃል እኔ ሰው ማግባት ነው የምፈልገው መኪናና ቤት ወይም ሱቅ አግብቼ አልቃጠልም አንተም ብትሆን ተጠንቀቅ ሰው አግባ አልያም ዘመንህ በሙሉ ስትነድ ትኖራለህ ብዬው ተሰናበትኩት፤ የሚገርማችሁ ይህ በሽታ ብዙ ሰዎችን ነው እየለከፈ ያለው ሴቶች እቶቻችንም ቢሆኑ የጋብቻ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ምን አለው ሆኖዋል የመጀመሪያ ጥያቄያቸው፤ እርግጥ ነው ትዳር ሲያዝ መተዳደሪያ የሚሆኑ ነገሮች ለምሳሌ ቤት፤ ሥራ ሌሎችም ሌሎችም ያስፈልጋሉ፤ ግን የትዳር መሰፈርት ሆነው ሊቀርቡ አይገባቸውም ቀጣይ ጉዳዮች እንጂ፤ ለትዳር መሰፍርቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የቆመ እውነተኛ ፍቅር ነው፤ ቆየት ብሏል አንድ ጋዜጣ ላይ ያነበብኩትን ልንገራችሁ፤ ትዳር ማለት የገቡበት ለመወጣት ያልገቡበት ደግሞ ለመግባት የሚጣደፉበት ተቋም ነው ይላል፤ አባባሉ አስደንቆኛል። ወገኖቼ እንዴት ያለ ነገር ነው በእኛ (በቅዱሳን) ትዳር እንዲህ መሆን አለበት እንዴ? በእርግጥ ከላይ ላሳያችሁ በሞከርኩት መንፈስ ወደ ትዳር ለሚገቡት ሲሰራ ይችላል፤ እናንተስ ምን ትላላችሁ በተበላሸ ዓላማ የሚመሰረቱ ጋብቻዎች በእርግጥ ጸንተው ይኖራሉ? መሠረታቸውስ ትክክል ነው? ትዳሩስ ትዳር ይሆናል? በፍጹም ትልቅ ኪሣራ ነው። በእንደዚህ ያለ መሻት ላይ የሚቀለሱ ጎጆዎች በሙሉ የተሳሳቱና ዓላማቸውም ተራ ነው፤ ደግሞም ጌታ ለትዳር ካለው ሃሳብ ጋር በሚቃረን መንገድ ወይንም በጠማማ ዓላማ የተጀመሩ ስለሆኑ ባይፋቱ እንኳን ትዳር ሲኦል ሆኖባቸው ዘመናቸውን ይጨርሳሉ፤ ጌታ ከዚህ ይጠብቀን።

እንግዲህ ነገሮቹ እንዲህ ከሆኑ ታዲያ ሰዎች ትዳር ከመያዛቸው በፊት ምን መረዳት አለባቸው የሚል ወሳኝ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፤ በዚህ ሃሳብ ዙሪያ ሰፋ ያለ ነገር ማለት ቢቻልም እስኪ ለግንዛቤ ይሆነን ዘንድ አንድ ሶስት መሠረታዊ ነጥቦችን እንይ።

*1. አንድ ሰው የሚያገባት ሴት (ሚስቱ) እነደ እግዚአብሔር ቃል ልዩነት በሌለው አንድነት የራሱ አካል መሆኗ ገብቶት እንደ ራሱ ሊወዳት፤ ሊያፈቅራትና ሊጠነቀቅላት ደግሞም ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ ሁሉ እርሱም እንዲሁ ሊሆንላት እንደሚገባ ማወቅ፤*

*2. የእግዚአብሔር ቃል መልካም ሚስት ለባሏ ዘውድ ናት እንደሚል ለእሱ ውበትና ሞገስ ደግሞም በረከት እንጂ አልጋ ለማንጠፍና ቤት ሞቅ ሞቅ ለማድረግ ወይም ከዘመኑ ችግር ማምለጫ እንድትሆን በማሰብ መሆን እንደሌለበትና ከእርሱ እኩል በቤቷ መብት እንዳላት ማወቅ፤*

*3. እግዚአብሔር ትዳርን ሲሰጥ ለጋብቻ ከፍ ያለ አክብሮት እንዳለው በውስጡ ትልቅና ዘላለማዊ ዓላማ እንዳስቀመጠበት በመገንዘብ ትዳርን ለሌሎች ተራና ድብቅ አላማዎችን ለማስፈጸም መመስረት እንደሌለበት ማወቅ ናቸው፤ በእርግጥ ሰው እነዚህን እውነቶች አውቆ በንጹህ ህሊና በእውነተኛ ፍቅር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ጋብቻን ቢይዝ የተሳካ የትዳር ህይወት ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ።*

*እስኪ ምሳሌ ይሆነን ዘንድ ፍጹም ልዩነት በሌለው አንድነት ውስጥ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠውን ጋብቻ እንይ፤ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፤ ስለዚህ ሰው አባቱን እና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ዘፍ 2፡24 ይህንን ክፍል ስናይ በፍጹም ሊለያዩ የማይችሉ አንድ ሥጋ መሆናቸው ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። አንድ ጊዜ ለራሴ እንዲህ አልኩ እግዚአብሔር አዳምን ብቻውን ፈጥሮት እንደገና ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ያለው ተሳስቶ ነው እንዴ? ደግሞ ሔዋንን ከጎኑ በወሰዳት አጥን ሴት አድርጎ የሰራት ስህተቱን ለማስተካከል ነው እንዴ ብዬ ጠየኩ ለራሴ፤ የዚህን ጥያቄ መልስ ካገኘሁበት ቀን ጀምሮ በጌታ ሥራ በጣም ነው የተደነኩት፤ የሚገርማችሁ እግዚአብሔር በሥራው ፍጹም ጻድቅ ነው። ታዲያ ለምን ይህንን አደረገ ትሉ ይሆናል፤ ነገሩ እንዲህ ነው። በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል*

በሄኖክ ተሾመ

## ጉዳዩ ከልብ ነው

የሰው ልብ እጅግ ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል? ይላል የእግዚአብሔር ቃል። ታዲያ ይህንን ስናይ የልብ ጉዳይ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ነው የሚያሳየው፤ ደስ የሚለው ግን ጌታ የሰውን ልብ አብጠርጥሮ ያውቀዋል፤ በህይወቴ ይህንን ሳስብ ደስ ይለኛል፤ ምክንያቱም እከሌ እንዲህ ያለው እንዲህ ሊል ፈልጎ ነው፤ አይልም ማን ለምን ምን እንደሚያደርግ ያውቃልና፤ እስኪ ለመልእክቱ ማዕከል ያደረኳቸውን የሁለት ሰዎች ታሪክ እንይ።

እነሆ ደሃ ናት መበለቲቱ ድህነቷ ሃገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው የተመሰከረላት ግን የማትበገር እጇን የማትሰጥ ችግሯን ለመሙላት ብላ ከቤተ ክርስቲያን የማትቀር ታዲያ እንደልማዱ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዳ ሳለ ያለ አቅሟ ከባለጠጎች ጋር ተሰለፈች። ጉድለቷን በመዝገብ ልትሞላ ሃብታሞቹ ከገንዘባቸው ብዛት የተነሳ በኩራት ተዝናንተው በመዝገብ እየጣሉ ዞር ዞር ብለው ሰው እያዩ ሲወጡ የእርሷ ተራ ደርሶ መዝገቡ ጋር ስትደርስ፤ አሁን አንዳንዶቻችን ወይ በስራ ማጣት አሊያም በሌላ ምክንያት የምንሰጠው መባና ምናልባትም አስራት ትንሽ ብር ወይም ሣንቲም ሲሆን ከጎናችን ያለው ሰው ብዙ ሲሰጥ እያየን በመሳቀቅ እናልፍና የያዝናትን ደብቀን የአሥራት እቃ ውስጥ እጃችንን ታች ድረስ አስገብተን ሣንቲሙ ድምፅ እንዳያሰማ እንደምንጥል ሳይሆን፤ ያለፍርሃት በመተማመን የእነርሱን ሣታይ አንድ ሣንቲም የሚያክል ሁለት ናስ ጣለች።

ይሄኔ ነው ታዲያ በመዝገብ አጠገብ ተቀምጦ አጣጣል ሲያይ የነበረው ጌታ ባለጠጎቹ ያንሁሉ ገንዘብ ሲያፈሱ ምንም ሳይመስለው በዚህች መበለት የእምነትና የልጋስ አጣጣል በጣም ከመደነቁ የተነሣ ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ ኑ ላሳያችሁ ይህችን የደሃ ሃብታም በመዝገቡ ውስጥ ከጣሉት ከባለጠጎቹ ሁሉ ይልቅ እርሷ አብልጣ ጣለች፤ ያለ የሌለ ንብረቷን አሟጣ ትዳሯን ሁሉ ጣለች፤ ብሎ ተደንቆ መሠከረላት! (ማር 12፡41) ሌለኛዋ ደግሞ የተስፋ ቃል የሌላት ከነናዊት ናት ጠንካራ የጀመረችውን እስክትጨርስ ወደ ኋላ የማትመለስ ምንም ነገር ይምጣ ቆማ የምትጋፈጥ ግን ልጇን ጋኔን ክፉኛ ይዞ የሚያሰቃይባት ጌታ ወዳለችበት አገር በመጣ ጊዜ ወደ እርሱ ተጠግታ የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ ልጄን ጋኔን ያሰቃየዋል፤ እያለች ድምጿን ከፍ አድርጋ ተማጠነች፤ ጌታ ግን አንዳችም አልመለሰላትም ዞርም ብሎ አላያት ሠምቶ የናቃትም መሠለ ከነናዊቷ በቃ ዝም አለኝ ተጠይፎኛል ብላ መች በቀላሉ ተስፋ መቁረጥ ታውቅና እየተከተለች በእምነት ጬኸቷን ለቀቀችው በዚህ የተረበሹ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ጌታ ቀርበው ከኋላችን ትጮሃለችና እባክህ አሰናብታት ቢሉት ጌታም ቀበል አድርጎ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በስተቀር አልተላኩም፤ እያለ ሲመልስላቸው እርሷ ቀረብ ብላ ጌታ ሆይ እርዳኝ እያለች በፊቱ ሠገደች፤ ኢየሱስም አይቻልም ላንቺ አይደረግም የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለቡችሎች መጣል አይገባም ሲል፤ እርሷ መች የዋዛ ሆና በቀላሉም በንግግርና በቃል የምትሰናከልም አልነበረች ከጌታ ጋር እውነትን ይዛ ሞገተች እንዲህም አለችው አዎ ጌታ ሆይ አንተ

አትሳሳትም ልክ ነህ እኔ ተስፋ የለኝም የእስራኤል ወገን አይደለሁም አንተ እንዳልከው ቡችላ ነኝ አልተሳሳትክም ግን አንድ ጊዜ ስማኝ ልናገር ጌታ ሆይ ቡችሎችም እኮ ከጌቶቻቸው መዓድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ አለችው በዚያን ጊዜ ኢየሱስም በጣም በመደነቅ አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው እንደ ወደድሽ ይሁንልሽ ብሎ አሰናበታት እያሉ በጠየቁት በደቀ መዛሙርቱና በሚከተሉት ፊት መሠከረላት። (ማቴ 15፡21-28)

ጌታ በምድር ይመላለስ በነበረበት ጊዜ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው በብዙ ሰዎች ህይወት ተደንቋል መደነቁ መልካም ነው ነገር ግን ወሳኙ ነጥብ ጌታ የተደነቀበት ምስጢር ምንድነው የሚለው መሆን አለበት መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለትምህርታችን ነው ይላልና ከእነዚህ ሁለት ሰዎች የህይወት ምስክርነት ምን እንማራለን? በእርግጥ ሁለት ዲናር የሰጠችው መበለት ከሌሎች የበለጠ ሰጥታ ነውን? ጌታ የተደነቀባት ከሁሉ አብልጣ ሰጠች ያላት አይደለም ከእርሷ በመቶ እጥፍ የሚበልጥ የሰጡ ነበሩ፤ ነገር ግን እዚህ ጋር የሚያሳየው ስጦታ ከብዛትና ከማነስ ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከልብ ጋር መሆኑ ነው ያች ሴት ሁለት ዲናር ስትሰጥ ከልቧ ከነፍሷ ለጌታና ለእግዚአብሔር ቤት ካላት እውነተኛ ፍቅር የተነሳ ያላትን ሁሉ ነው የሰጠችው ይህ የሚያሳየው ልቧም ገንዘቧም ከጌታ ጋር መሆኑን ነው ታዲያ የጌታ በዚች ሴት የመደነቁ ምስጢር ይህ ነበር ለካ ጌታ ስጦታችንን ብቻ ሣይሆን ልባችንንም ያያል ማለት ነው አዎ በእርግጥ ያያል፤

ያችም ከነናዊት ሴት በእምነቷና በታጋሽነቷ ጌታን እጅግ አስደነቅዋለች ጌታ ከዚች ሴት ጋር ተስፋ አስቆራጭና እልህ አስጨራሽ ቃለ ምልልስ አድርገዋል፤ ሴትየዋ ግን ከላይ እንዳየነው የአቋም ሰው ነበረችና እስኪ ቢሳካልኝ ብላ አልነበረም ወደ ጌታ የመጣችው ሊፈውስ እንደሚችል እርግጠኛ ሆና ነው። ትሰጠው በነበረው መልስ ልቧ ምን ያህል ጽኑ እንደሆነ አያት ከዚህም የተነሳ አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው አላት፤ ልብ በሉ እዚህም ጋር የጌታ የመደነቁ ምስጢር የሴትየዋ የልብ እምነት ነው ከሱ ሌላ ማንም ሊያድን፤ ሊፈውስ አይችልም የሚል የልብ ጽኑ አቋም ነበራት።

እና እኛም በዚህ ዘመን ልናስተውለው የሚገባን ጌታ የልብ አምላክ መሆኑን ነው፤ የውስጣችንን ያውቃል ስለዚህ ስጦታችንን ከልብ፤ እምነታችንን ከልብ፤ በማድረግ ጌታ በህይወታችን ደስ እንዲሰኝ ልናደርግ ይገባል። ሁላችንንም ጌታ ይርዳን።

ከሃብታሙ አስረስ

## *የሁለት ዓለም ሰዎች*

ይህ የሚታው ከማይታየው ነው፤ የሚታየው ለማይታየው ይገዛል፤ በጣም የሚደንቀው ደግሞ የማይታየው ለሚታየው ስልጣን ሰጥቶት የሚታየው የማይታየውን ሌላኛውን ዓለም ይገዛል፤ ይህ በመንፈሳዊ ዓለም የሚካሄድ አስደናቂ የአገዛዝ ጊደት በአንዱ በተገለጠው ዓለም ነዋሪ ለሆኑ ሁሉ የእንቆቅልሽ ጫወታ ሊመስል ይችላል።

ሆኖም እነዚህ የሁለት ዓለም ነዋሪዎች ሁሉን ይመረምራሉ እነርሱ ግን በማንም አይመረመሩም ሞኞች ሲመስሉ ብልህ ያጡ ሲመስሉ ባለ ጠጎች ናቸው፤ በማይታየው ዓለም ያለውን የጠለቀ አሰራር በተሰጣቸው አስደናቂ የመገናኛ መስመር ሲረዱ እንደሞኝ የቆጠራቸው የአንዱ የተገለጠው አለም ነዋሪ ይህ ምትሃት ሊሆን ይችላል በማለት እንደዘመበት ያየዋል የምናየውንም ሆነ የማናየውን ግዙፉን አለም በቃሉ የፈጠረ ለዘለአለም በማይናወጥ ዙፋኑ ላይ ያለ ልዑል እግዚአብሔር ይህንን ታላቅ መንፈሳዊ ምስጢር ካላበራለት ሰው በገዛ ማንነቱ ያውቀው ዘንድ ማን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር የሰው ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነው ይላልና፤ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ወይም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርና ህገ መንግሥት ነው ጨለማውም ሆነ ብርሃኑ በእርሱ ይለያል። እግዚአብሔርን የሚፈልጉት በ እርሱ ያገኙታል። ጥበበኞችና ብልሆች ከእርሱ ጋር ይስማማሉ ክፉውም ደጉም ትንሹም ትልቁም ነገር ሁሉ በእርሱ ፍንተው ብሎ ይታያል ፤ እነዚህ የሁለት ዓለም ሰዎች መተዳደሪያቸው ይህ ቃል ነው። ለዚህ ቃል ሲገዙ ሠራዊት በዙሪያቸው የለም፤ መድፍ አልተደገነባቸውም፤ ግን ይወዱታልና በፍቅር ይገዙለታል እርሱ ደግሞ ሁሉን ያስገዛላቸዋል አቤት ክርስትና ለባለአእምሮ ጨዋታ ለመንፈሣዊ ሰው ግን ክብር፤

ልዑል እግዚአብሔር በግርማ ሞገሱ ከፍ ባለ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ሁሉን ይገዛል ምድር የእግሩ መረገጫ ሰማይ ዙፋኑ ነው ታዲያ ሞኝነት በሚመስለው በቃሉ አምነው ለዳኑ ሁሉ ደግሞ የልጅነት ስልጣን ሰጥቷቸዋል። ሉቃስ 9፥1 እነርሱም ከእርሱ ጋር በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ተቀምጠው የማይታየውን ሌላኛውን ዓለም ይገዛሉ ኤፌ 2፥1፤ ክርስትና ይሉሃል ይሄ ነው፤ የስም ጉዳይ አይደለም ክርስቲያን የሰማዩንም የምድሩንም ኑሮ በመኖር ይገለጣል፤ የቀደሙት የአባቶቻችን ታሪክ ይህንን ያሳያል።

ኖህ ይኖር በነበረበት ዘመን የሰው ልጅ ይህንን ክቡር ሕይወት ሳይገባው ሲያጣጥል ሞኝነት በተባለው ጥበቡ ተመክቶ እግዚአብሔርን ሲዳፈር ሐጢአትን

እንደውሃ ሲጨልጥ ያ አልበቃ ብሎት እግዚአብሔር ማን ነው? ካለ እራሱን ይግለጥ፤ እያለ በትዕቢት ሲሞላ ከልዑል አምላክ ትእዛዝ ወጣ ኖህ በኑሮው ጻድቅ ነበረና ሊጠፉ ካሉ ጋር አብሮ እንዳይጠፋ ማምለጫ የሚሆነው መርከብ እንዲሰራ ትእዛዝ ተሰጠው፤ መርከብ መስራት በጀመረ ጊዜ ሁሉ ሰላም ነበር እና የአንዱ የተገለጠው ዓለም ነዋሪዎች ያፌዙ ይሳለቁበት ጀመር። ሆኖም ኖህ ግን የሁለት ዓለም ነዋሪ ነበር። እና በተሰጠው ሌላ የመገናኛ መሥመር የሰማውን እውነት ተቀብሎ ማምለጫውን በትጋት ይቀጠቅጥ ነበር።

**የጥፋት ውኃ በመጣ ጊዜ እንደሞኝ የተቆጠረው ኖህ ብልህ ብልህነን ብለው የሰነበቱት ሞኝ ሆነው ተገኙ።**

ኖህም ከላይ በደረሰው መለኮታዊ ትእዛዝ ወደ መርከቡ ሊገቡ የሚገባቸውን አስገባ በጣም የሚደንቀው ታዲያ መርከቡን የዘጋው ግን እግዚአብሔር ነው። ምን ትሉ ይሆን? የእናንተን ለእናንተ ተውኩት እኔ ግን ተአምር ነው የሆነብኝ መርከቡን የሰራው ኖህ የዘጋው ግን እግዚአብሔር ይህ በራሱ ትልቅ ምስጢር ነው። ታዲያ ያ የመጣው የጥፋት ጎርፍ ግንኙነታቸው ከተገለጠው ከአንዱ ዓለም ጋር ብቻ የሆኑትን በሙሉ ጠርጎ ወሰዳቸው የኖህ መርከብ ከፍ ከፍ ስትል እነርሱ ዝቅ ዝቅ እያሉ ሄዱ የጥፋት ውኃ በጨመረ ቁጥር ኖህ እና የጠፊው ዓለም ልጆች ልዩነታቸው እየሰፋ ሄደ፤ የሕይወት እስትንፋስ ያለው ሁሉ ከምድር እስኪጠፋ ድረስ የመከራው ዝናብ እጅግ እያየለ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ዘንቦ ሲያበቃ ሁሉ ከውኃ በታች ተቀብረው ያየ ሁለት ዓለም ሰው ግን በአራራት ተራራ ላይ በከፍታ ተገኘ። ዘፍ 6 - 8

እንዲሁም የሶሪያው ንጉስ በቤተ መንግሥቱ ቁጭ ብሎ በእስራኤል ላይ የሚመከረውን ክፉ ምክር ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት በእስራኤል ንጉሥ ዘንድ እየደረሰ ምክሩ ከንቱ ይሆንበታል ይህ ያስቆጣው የሶሪያው ንጉሥ ሹማምንቱን ሰብስቦ ከኛ መካከል ምስጢር የሚያባክን ሰው አለ፤ እያለ በሹማምንቱ ላይ ቢደነፋ ከመካከላቸው አንዱ እንዲህ አለው ንጉሥ ሆይ ነገሩ አንተ እንደምታስበው አይደለም በእስራኤል ዘንድ አንድ የእግዚአብሔር ሰው አለ እኛ እዚህ የምንመክረውን ምክር ሁሉ አምላኩ ይገልጥለታል አለው አቤት ክርስትና እንዴት ድንቅ ነው፤ እንደ ሥጋ ለባሽ በምድር ይኖራል እንደመንፈሳዊ ደግሞ ሰማያዊውን ኑሮ ይኖራል ክርስትና ይህ ነው የስም ጉዳይ አይደለም፤ ክርስትና ከስም ያለፈ የሁለት ዓለም ገጽታ ያለው ድንቅ ሕይወት ነው ያ የዚህ የተገለጠው የአንዱ ዓለም ነዋሪ ንጉሥ ኤልሳዕን አምጡልኝ ብሎ ሠራዊት ላከ ምነውሳ ይህ ንጉሥ ማስተዋል አጣ ያሰኛል ምክንያቱም ያንን ምስጢር የገለጠለት አምላኩ ይህንንም ይገልጥለታል ብሎ አለማሰቡ የሚደንቀው ነገር ኤልሳዕን ሊይዙ የመጡት የሶሪያ ሠራዊቶች በሙሉ ያለ ምንም ተኩስ ያለ ምንም ደም መፋሰስ ተማርከው በእስራኤል ቤተ-መንግሥት ውስጥ ተገኙ። **ድንገት የታወረ ዓይናቸው ያሉበትን ቢቃኙ ታዳኙ አዳኝ ሆኖ አገኙት አቤት የሁለት ዓለም ሰው ኑሮ ልዩ ነው፤ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።** 2ኛ ነግ 6፥8-20

ውድ የእግዚአብሔር ሰዎች ክርስትና ይህ ነው። የሰማዩንም የምድሩንም ኑሮ መኖር። አንድ እውነት ልንገራችሁ በመሰል ሥም የሚጠሩ በአብ ዘንድ ግን የማይታወቁ ግንኙነታቸው ከዚህ ከተገለጠው ከአንዱ ዓለም ጋር ብቻ የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉ ክርስትና የስም ጉዳይ አይደለም የመዳን ትልቅ ምስጢር የያዘ ክቡር ሕይወት እንጂ ክርስትና ዳግመኛ በመወለድ የሚገኝ ሕይወት ነው፤ ያልወለዱትን ልጅ ልጄ ነው ማለት እንደማይቻል ሁሉ ዳግመኛ ካልተወለድን የእግዚአብሔር ልጅ (ክርስቲያን) መሆን አንችልም። ክርስትና የውልደት ጉዳይ እንጂ የውርስ አይደለም፤ ከአያት ከቅድመ አያት የመጣ ተብሎ አይወረስም በክርስቶስ በማመን ግን ክርስቲያን መሆን ይቻላል።

ክርስትና ባሕልም አይደለም ከዘላለም ሞት ማምለጫ እንጂ በአዋጅ ነጋሪ ማንነትን መግለጥ አያስፈልገውም በኑሮ ግን ይገለጣል፤ ልክ ስትኖር የሚያዩህ ሁሉ ይህ ሰው ኑሮውና ንግግሩ ልክ እንደክርስቲያን ነው ይሉሃል።

በአንድ ወቅት አንድ የእግዚአብሔር ሰው ክርስትና ይኖሩታል እንጂ እይለፈልፉትም … ሃቅ አይደል?

አይገርማችሁም ስመ ክርስቲያን ሁሉ ክርስቲያኖች አይደሉም ክርስቲያን በክርስቶስ አምኖ የዳነ አበሳው የተወገደለት የላዩንም የታቹንም ኑሮ የሚኖር ነው። በምድር የምትኖር ነህ ብለው ሲያስቡህ አድራሻህ በሰማይ በአብ ቀኝ ያውም ሰማያዊ ዜጋ ሆኖ ይገኛል 1ጴጥ 1፥23 ። ምንም የማታውቅ ምስኪን ስትመስል ሰማያዊ ምስጢር ትገልጣለህ በዚህ ተደንቀው አማልክት ነህ ብለው ሊሰግዱልህ ሲመጡ ሰው መሆንህን ትናገራለህ የሐዋ 14፥8-15 ሥጋ ለባሽ ነህ በመንፈሣዊው ዓለም ግን ባለ ስልጣን ሉቃ10፥19 ይደንቃል ይህ ክርስትና የአደባባይ ምስጢር ነው። በአደባባይ የተከናወነ በአደባባይ የሚነገር ነገር ግን ለብዙዎች የተሰወረ ለበራላቸው አቤት ክብሩ ለተሰወረባቸው ግን አናጢዎች የናቁት የማዕዘራ እራስ ድንጋይ ዋ! ክርስትና እንዴት እንግለጠው! ከዘመናት ዘመናት እየተሸጋገረ በሕይወትና በደም ዋጋ እዚህ የደረሰ አሁንም በጽድቅ ለሚኖሩ ዋጋ የሚያስከፍል በፍጻሜው ግን ሊተመን በማይችል ዋጋ ብድራቱን የሚከፍል አስደናቂ ሕይወት ነው ዮሐ.ራ 22፥12 ። ክርስትና ይህ ነው የተገለጠ ምስጢር ለሰሚው ግራ የሰማይ ብርሃን ለበራላቸው ግን ድንቅ እንግዲህ እናንተ መሳዮቼ ለአንዱ ለተገለጠው አለም ነዋሪዎች ቅብዥርዥርታ የሆነውን ሕይወታችንን በክብር እንያዝ።

በሄኖክ ተሾመ

## የምለው አለኝ !!

የምለው አለኝ የምጣጥፈው
በፍቅሩ ጉልበት ተሸንፌአለሁ
ይኸው ማርኮኛል እኔም ጋ ደርሶ
እረስርሻለሁ ፍቅሩ ውስጤ ፈሶ

አገኘሁ ፍቅር በአፍላ እድሜዬ
ብዙም ሳልደክም በጉብዝናዬ
የዘለአለም መጠለያዬ
አሳርፎኛል ይክበር ጌታዬ

አልጠበኩኝም እንዲህ አለ ለካ
አሳየኝ ፍቅር የማይለካ
በማንም በኩል የማይተካ
የየሱስ ፍቅር ነፍስ የሚያረካ

ተማርኬያለሁ ገዝቶኛል ፍቅሩ
ለየት ብሎብኝ ካየሁት ሁሉ
ከዚህ የተነሳ ቃል ገብቻለሁ
ለሌላ ላልሆን እጅ አንስቻለሁ

አንዳንዴ ሳስብ ዞር ዞር ብዬ
ያሹኝ ነበሩ በጉዳናዬ
አሳለፍኳቸው ይለፈኛ ብዬ
ታድያ ይገርመኛል ይህ ውሳኔዬ
እሱን ግን ሳየው አልኩኝ ጌታዬ
ተደላደልኩኝ ተክፍሎ እዳዬ

ማነው በልቡ ፍቅር የራበው
የኃጢያት ሸክም ያንከራተተው
ጆሮ ያለው ይስማ እኔ ልንገረው
ከሞት የሚያድን ፍቅር የሆነው
የነፍሴ ጌታ ውዴ ኢየሱስ ነው

ከሣባ አዳሙ

## ሔዋንን ናፍቄ

ለብዙ አመታት ሔዋንን ናፍቄ
ጎድኔን ብዳብስ ትውጣ ትታይ ብዬ
መች እንደሱ ሆነ ተኛ አልኝ ገታየ
አቤት የአምላክ ሥራ እንዴት አስገረመኝ
ከእንቅልፌ ስነቃ ሔዋንን ሸለመኝ
እኔም ይህንን ሳይ ስለተገረምኩኝ
ጎድኔን መዳበስ መፈተሽ ጀመርኩኝ
የሚደንቀው ታድያ አንዱ ጎደለብኝ
ያኔ ነው የገባኝ ጌታ ያረገልኝ
ለካስ አጥንቴን ነው መልሶ የሰጠኝ

በሄኖክ ተሾመ

## ቃሌን አልዘነጋም !!

ቃሌ ምን ነበር የገባሁት ለእግዚአብሔር
ያኔ ሲያወጣኝ ከጨለማው ሀገር፤
ሊያቆመኝ ሲመጣ ሸላልሞ በክብር
በትንሿ ልቤ ሲወስን ሊያድር፤
ኧረ እንዴት ሊጠፉኝ ያኔ የወሰንኩት
በፍጹም ይሄንን አላደርግም ያልኩት፤
ይሄ ሆኖ ሳለ የልቤ ውሳኔ
ጠላት ግን ዘረጋ ወጥመድን በእኔ፤

ምን አለበት በሚል በሚያባብል ቃል
ይተርክ ጀመረ የሐጢያትን መብል፤
ጓደኞችሽን እይ በዓለም አምሮባቸው
ከዘመኑ ጋር ሲራመዱ አብረው፤
አንቺ ግን በከንቱ ሁሉን ነገር ትተሽ
ባላየሽው ነገር ተስፋን እየሰነቅሽ
ሳትጠቀሚበት በዚህ አፍላ እድሜሽ
ኢየሱስ ኢየሱስ እያልሽ ኋላ ቀረሽ
በጣም አሳዘንሽኝ ስንቱ አመለጠሽ፤

እያለ ሌት ተቀን እየጉተጎተተኝ
ወደ ኋላ እንዳይ መላልሶ መከረኝ፤
ሞከረ በጣሙን ተስፋዬን ሊቀማኝ
መስሎት ያልነቃሁኝ ምክሩ እንደማይጠቅመኝ፤
አልመለስም ፍጹም ከንቱ ወደ ሆነ አለም

ተስማምቶኛል ጌታ ምንም አልጐደለኝ
ወደፊት እጓዛለሁ ጌታዬ አለልኝ
ማንንም አልፈራም ተጠብቄያለሁኝ
ጠላቴም ይመልከት ወጥመዱ እንዳልያዘኝ
አሁንም ፀንቼ እጠብቃለሁኝ
በላይ በሰማይ ነው የተስፋዬ ክብር
ፍጻሜዬ አይደለም መኖር በዚች ምድር

ከሣባ ተስፋዬ

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በቦስተን

ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH BOSTON

88 TREMONT STREET, BOSTON, MA, 02108
T: 617-523-5058 F: 617-523-5058
www.eecBoston.org